# የሕፃናት የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ክትባት FAQ (በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች)




## 1፡፡ ክትባቱ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው?

**አዎ፣ ክትባቱ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው፡፡** የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ክትባት እድሜያቸው ከ5 እስከ 11 የሆነ ከ3000 በላይ ህጻናትን ያካተቱ ሰፊ የክሊኒካል ሙከራዎች ውስጥ አልፏል እና ምንም ከባድ የጎንዮሽ ጉዳቶች እንደሌላቸው ታይቷል፡፡ እንዲሁም በምግብ እና መድሃኒት አስተዳደር (FDA) እና የበሽታ መቆጣጠሪያ ማዕከላት (CDC) ጸድቋል፡፡

## 2፡፡ ክትባቱ ምን ያህል ውጤታማ ነው?

ክትባቱ እድሜያቸው ከ5 እስከ 11 የሆነ ህጻናት ውስጥ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ለመከላከል 90% ውጤታማ ነው፡፡

## 3፡፡ ልጄ ምን ያህል ዶዝ ይወስዳል/ትወስዳለች?

ክትባቱ በሶስት ሳምንታት ልዩነት የሚወሰድ የሁለት-ዶዝ አሰጣጥ ዓይነት ነው፡፡ እድሜያቸው ከ 5- እስከ 11-ዓመት ለሆነ የሚሰጠው ዶዝ የጎረምሳ/አዋቂ ክትባት አንድ-ሶስተኛ ነው፡፡

## 4፡፡ ሊከሰቱ የሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳቶች ምንድን ናቸው?

እድሜያቸው ከ12 እስከ 15 የሆነ እና Pfizer-BioNTech የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ክትባት የተሰጣቸው ህጻናት እድሜያቸው 16 እና ከዚያ በላይ የሆኑትን ከሚያጋጥመው የጎንዮሽ ጉዳቶች ጋር የሚመሳሰሉ የጎንዮሽ ጉዳቶች ነበራቸው፡፡ በጣም ሪፖርት የተደረጉ የጎንዮሽ ውጤቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፥

- ክትባቱ የተሰጠበት ቦታ የሚሰማው ህመም
- ድካም
- ራስ ምታት
- ብርድ ብርድ ማለት
- የጡንቻ ህመም
- ትኩሳት
- የመገጣጠሚያ ህመም

ልክ እንደ አዋቂዎች፣ ህጻናት በተለምዶ ከ1 እስከ 3 ቀናት የሚቆዩ የጎንዮሽ ጉዳቶች አላቸው፡፡

ልጅዎ የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ክትባት ከተሰጠው/ጣት በኋላ፣ እሱ/ሷ ህክምና የሚያስፈልገው አለርጂ ያለው/ላት እንደሆነ ለማየት ለ15 እስከ 30 ደቂቃዎች ክትትል ይደረግለታል/ላታል፡፡

## 5፡፡ ልጄ ሌሎች ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የጤና ጉዳዮች ወይም በፊት የነበሩ ሁኔታዎች ካለውስ/ካላትስ?

ለቤተሰብዎ እውቀት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ መስጠት እንደሚችሉ ለማረጋገጥ ከልጅዎ ሃኪም ጋር መነጋገር ሁልጊዜ በጣም ጥሩ ነው፡፡

## ልጆችዎ ክትባት እንዲወስዱ ለማድረግ እቅድ ያዘጋጁ፡፡

የክትባት ቦታን እዚህ ያግኙ፥ **vaccines.gov**፡፡